*ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ*

*Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity*

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*ፕሮግራም፥ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ*

*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band*

# <u>የሱዳኖችና የወያኔ ወታደራዊ ስምምነት</u>

**የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ**
**ነሐሴ 28 2006 ዓ.ም. የተላለፈ**

ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ፤ ሱዳኖችና ወያኔዎች የጋራ ወታደራዊ ውል መፈራረማቸውን ይፋ አድርጋዋል። የሱዳን የመከላካያ ባለሥልጣናት ከወያኔ ወታደር አላቆች ጋር አዲስ አበባ ላይ ተሰብስበው የተነጋገሩበት ዋናው የስምምነቱ ጭብጥ፤ **በአንድ የጋራ መከላከያ ዕዝ የሚታዘዝ ጦር ማዘጋጀት** እንደሆነ አስታውቀዋል። ይህ የጋራ ጦር፤ በመስከረም ወር ለስምሪት ብቁ ይሆናልም ተብሏል። የግዳጁ ስምሪት፤ በሁለቱ ሀገሮች የጋራ ወሰኖች አካባቢ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ ተጥቅሷል። የጋራ ስምምነቱ ዓላማ፤ ለዎያኔና ለሱዳኖች ፀጥታ አስጊ ናቸው የሚባሉትን ኀይሎች በጋር ለመመከት እንደሚሆን ያትታል።

የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ትኩረት የሚያጠነጥነው፤ በሁለት ምክንያቶች ዙሪያ እንደሆነ ይናፈሳል። አንደኛው፤ ወያኔን ተቃውመው የሚንቀሳቀሱት ኀይሎች፤ የሱዳንን መሬትና ወሰን በመጠቀም ጥቃት እንዳይሰነዝሩ ለመከላክ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፤ የዓባይን ግድብ ለማደናቅፍ ከግብጽ በኩል የሚሰነዘረውን ጥቅት በጋራ ለመመክት የሚል ነው። የዐባይ ግድብ ሥራ እየተካሄደ ያለው ከሱዳን ጠረፍ አርባ ( 40) ኪሎ ሜትር ርቀት ብቻ ነው። ግብፅ፤ ኢትዮጵያን ስታጠቃ፤ ሱዳን፤ ግብፅን ተጻርራ በመቆም፤ የኢትዮጵያን ጥቅም ታስጠብቃለች የሚለው የወያኔ ኅልም፤ የክፍለ ዘመኑ ስላቅ እንደሆነ፤ የፖለቲካ ታዛቤዎች የሰሞኑ ሽሙጥ ሆኖ ሰንብቷል። ጤናማ አዕምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ፤ ይህንን የፕሮፓጋንዳ ፌዝ፤ ወራቱ ያለፈበት፤ የተበላ ዕቁብ ነው ብሎ ፈርጆታል።

ሱዳን ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነጻ ከወጣችበት 1950 ዎቹ አንስቶ፤ የመጀመሪያው ጠቅላይ ምኒስትር ከነበረው ከእስማኤል አል ዛሃሪ ጀምሮ፤ እስከ አሁኑ መሪዋ አል በሽር ደረስ፤ ኢትዮጵያን ሲጎዱ የነበሩ ናቸው። በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ በመግባት፤ ተገንጣዮቹን በመርዳትና በማደራጀት፤ የጦር ማሳሪያና ሥልጠና በመስጠት፤ የፕሮፓጋንዳና ዲፕሎማቲክ ትብብር በመለገስ፤ ጉዳት አድርሰውብናል። ወያኔ አዲስ አበባ፤ ሻዓቢያም አስመራ እንዲገቡ አድርገዋል። ለሀገራችን ነጻነትና ልዕልና መደፈር ያላሰለሰ በደል ፈጽመዋል። የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመድፈርና ሕዝቧንም በመናቅ ተዘርዝሮ የማያልቅ ጥቃት ፈጽመዋል። በሱዳን ሀገር በስደተኝነት የተጠጉትን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን ሳይቀር፤ ለወያኔ አሳልፈው በመስጠት አስጨፍጭፈዋቸዋል። ብዙ የኢሕአፓ አባላትንና ከሀገር ወዳዶች፤ ደግሞ እነ ሻለቃ አጣናው ዋሴን፤ እንደ ዋቢ መጥቀስ ይቻላል !

ከጥቂት ወራት በፊት፤ ወያኔ ዓመታዊ በዓሉን በመቀሌ ከተማ በአከበረበት ሳምንት፤ የሱዳኑ ፕረዝደንት ኤል በሽርና የሱድን ብሄራዊ ፀጥታ ሹም፤ መቀሌ ከተማ በዕንግድነት ተግኝተው አበረው ጨፍረዋል። ይህ ድርጊት ወያኔዎቹ ወደፊት ትግራይን አስገጥለው ነጻ ሪፑብሊክ ሲመሰርቱ፤ ቀድመ ዕውቅና እንደመስጠት ተቆጯል። በተጨማሪም፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ መናቃቸው የቱን ያኅል ፈር የለቀቀና ድፍረታቸውም ወሰን ያላፈ መሆኑን ይመስክራል።" ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ነውና ከሞኝ በራፍ ሞፈር ቆርጠው ሄደዋል ።" ጥቃት የደረስባት ሀገርና ለውርደት የተዳረገው ሕዝቧም የደም እምባ ያለቅሳሉ። ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢጨንቀው፤

**" *ዐይኔ ጉድ አየ፤ ክፉ ዘመን ደርሶ ፤***
***የጥቃት ወጋግራ የውርደት ምሰሶ* "**

በማለት ምሾ ይደረድርል። የሱዳን መሪዎች ከወያኔ ጋር ቢተባበሩ አይደንቀንም። ሁለቱም ድርና ማግ በመሆን ሀገራችንን እያጠፉ ናቸውና!

በሌላ በኩል ግን፤ " ሸማ እንደፈርጁ ይለበሳል " እንዲሉ፤ የሱዳንን ሕዝብ፤ ከሱዳን መሪዎች ለይቶ ማየት፤ አግባብነት ይኖረዋል። በሁለቱ ሕዝቦች መካከል፤ የቆየ መልካም ጉርብትና ነበረ፡፡ አሁንም ያው ነው። ተፈጥሮ ያስገኘው ይህ ጉርብትና ይቀጥላል።ይኖራልም። የሱዳን ሕዝብ፤ ደግና ዕንግዳ ጠቅባይ ነው። ችግር በገጠመን ጊዜ ተባባሪያችን ነበር። ስንሰደድ አስጠግቶናል። የሙሶሊኒ ወረራ ባስከተለው ስደት ምክንያት በሽ የሚቆጠሩ የሀገራችን ስድተኞችና አርበኞችን አስጠግቷል፡፡ ረድቷል። ክፉውን ዘመን በዚያ እንዲያሳልፉ አድርጓል። የኢትዮጵያ አርበኞች ጣሊያንን ለመውጋት ካስቻላቸው ኅይል አንዱ ፤ በሱዳን ጠረፍ በሚያስገቡት ጦር መሳሪያ እንደነበር ሁሉም የሚያውቀው ነው። አየለ አባ ጓንዴን፤ ህይወት ኅዳሩን፤ ገሪማ ታፈርንና ይልማ ሺበሺን የአርበኝነት ሙያና የሱዳንን ወሰን እየተጠቀሙ፤ የጦር ማሣሪያ ለተዋጊው ኅይል ማስተለለፍን ዘከሮ ማለፍ ይቻላል። እኛ ኢትዮጵያውያን፤ ዐርበኞቻችንን አንረሳም። ወዳጅና ጠላቶቻችንንም ለይተን እናውቃለን !

ከአለፉት አርባ ዓመታት ጀምሮም ከደርግ ጭፍጨፋ እስከ ወያኔ ዕልቂት ድረስ የተካሄደውን ብሄራዊ ጥፋት በመሸሽ የሚሰደደውን፤ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በማስጠጋት፤ የርኅራኄ ተግባር የፈጸመ ታላቅ ሕዝብ ነው፤ የሱዳን ሕዝብ ! ኢትዮጵያውያን ስደተኞች፤ ከደርግና ከወያኔ የሚደርስባቸውን ግድያና እስራት ለማምለጥ፤ የሱዳንን በረሃ እያቋረጡ ህይወታቸውን አትርፈዋል። በርካታ ኢትዮጵያውያን፤ ሱዳንን የማምለጫና የመሸጋገሪያ ድልድይ በማደረግ፤ ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገሮች በመሰደድ፤ ህይዎታቸውን አትርፈዋል።

በሁለቱ ሕዝቦች መካከል፤ የባኅል ግንኙነቶች አሉ። የንግድ ለውውጦች፤ የስፖርትና ሙዚቃ መድረኮች ህያው ናቸው። ዝነኛው የሱዳን ዘፋኝ መሀመድ ወርዲ "ኢትዮጵያ ወ ሱዳን፤ ኣክዋን ኣክዋን " ኢትዮጵያና ሱዳን መንድማማቾች ናቸው ! ብሎ በማዜሙ የብዙዎችን ልብ ማርኳል። የኢትዮጵያ ቅርስ የነበረውም አለማየሁ እሸቴም በበኩሉ፤ በዐረብኛ ቋንቋ፤ "ሰባታ - አሸር ሰንአ " አስራ ሰባት ዓመታት ! ብሎ በማዜሙ የካርቱምን ሕዝብ ልብ በልቶት ነበር። ሕዝብ- ለሕዝብ ወዳጅነትን እንጅ ባላንጣነትን አያስተናግድም ። የሱዳንና የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሠላም መኖርን ይመኛሉ። ሁሉ ጊዜም ይኖራሉ ። ኤል በሽርና ወያኔ ግን ያልፋሉ። ይጠፉሉ።

ይህ ሃቅ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የሱዳን መሪዎች ግን የሚፈጽሙብንን ብሄራዊ በደል በለሆሳስ ፤አንመለከተውም። አንረሳውም ! የወጋ ሊረሳ ይችል ይሆናል። የተወጋ ግን ሊረሳ አይችልም። መበቀል ባያስፈልግም ፤ ካጥቂዎች መከላከል ግን ግደታ ነው። በየጊዜው፤ የሱዳን መሪዎች፤ በማያገባቸው በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ በመግባት በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን በድለዋል ። ከኣጥፊዎቿ ጋር እየተባበሩ ፤ ሀገራችንን እንድትጠፉ የማያደርጉት ዕኩይ ድርጊት የለም ። እኛ ግን "ምን አደርግናችሁ ? " አመልና ኤ ! " እንላቸዋለን ።

በሀገራችን ደሞክራሲያዊ ሥርዓተ- መንግሥት ተመስርቶ፤ የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁ ሀገር -ወዳድና ለህግ ተገዥዎች የሆኑ መሪዎች ከመጡ፤ ከባዕድ ሀገር ጋር ወታደራዊ ውል የሚፈረምበት አስገዳጅና አጣዳፊ ምክንያትም ከተከሰተ፤ ወታደራዊ ውል ይሁን ሌሎችንም ውሎች መፈራረም ይቻል ይሆናል። ከባዕድ ሀገር ጋር ወታደራዊ ውል ለመፈራረም አስገዳጅና አስቸኳይ ሁኔታዎች ቢፍጠሩም እንኳን፤ በህግ የተቋቋመ የሀገሪቱ ብሄራዊ ምክር ቤት ( ሸንጎ) እንዲያጸድቀው ግድ ይላል። ዛሬ፤ ያ ሁኔታ የለም። ይህ ሁኔታ ሳይኖር፤ ከባዕድ ጋር ወታደራዊ ውል መፈራረም፤ የሀገሪቱን ልዋላዊነትና የሕዝብ ኅልውና አደጋ ላይ መጣል ይሆናል። ይህንን ለመናገር የሚቻለው ደግሞ ቀድሞውንም ቢሆን፤ ኢትዮጵያዊ ባኅርይንና ስብእናን የተላበሰ ሥርዓት አራማጆች ቢኖሩ ነበር። የወያኔ መሪዎች ደግሞ፤ ያ ባኅርይና ሰብዕና የላቸውም። እነኝህ ስብስቦች፤ ትላንት የሀገሪቱን አካል በማስገንጠል ወደብ -አልባ ያደርጉ ፍጥረቶች ናቸው። ታዲያ ዛሬ ከሱዳን መሪዎች ጋር የጦር ቃል- ኪዳን መፈራረማቸው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ አያስገርመው።

የኢትዮጵያንም ለምና ሰፊ መሬት ለሱዳን ያስረከቡ ለመሆናቸው ያደባባይ ምሥጢር ነው ። በዚህም ምክንያት በብዙ ሽ ሊቆጠሩ የሚችሉ ያካባቢው ነዋሪ የነበሩ ኢትዮጵያውያን፤ ከአጽመ-ርስታቸው ተፈናቅለዋል። ይህ እየታወቀ፤ የዛሬ ሳምንት አዲስ አበባ ላይ ከሱዳኖች ጋር የተፈራረሙት ወታደራዊ ውል ስምምነት ለምን ቅድመ-ዝግጅትና ድልዳል እንደሆነ መረዳት ፤ ለማንም የፖለቲካ ታዛቢና ተንታኝ ከባድ አይሆንም ። የወያኔ መሪዎች፤ የረዥም ጊዜ ዕቅዳቸውን ተግባራዊ ለማደርግ፤ ሌት- ተቀን ተግተው ይሰራሉ። የረዥም ዕቅዳቸውን መስፈጸሚያ እንዲሆናቸው እስካሁን የፈጸሟቸው ዋና ዋና ተግባሮችን እስቲ እንመልከት፤-

- ኤርትራን አስግንጥሎ ኢትዮጵያን ወደብ-አልባ ሀገር ማደርግ፤
- እጅግ ለምና ሀብታም የሆነውን የጎንደርን ፤ የወሎንና የዐፋርን አጎራባች መሬት ወደ ትግራይ ግዛት ማጠቃለል፤
- ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የሚያዋስናትን ርዥምና ሰፊ የሀገራችንን ግዛት ለሱዳኖች ማስርከብ፤ ብሎም፤ ትግራይንና ሱዳንን የሚያዋስን ዓለም አቀፍ ወሰን መፍጠር፤ አዲስ ካርታ መሳልና አዲስ ግዛት ማረጋገጥ፤

- ለወደ ፊቷ ፤ የትግራይ ሪፑብሊክ፤ ከሱዳንና ከኤርትራ ጋር ሊኖራት የሚያስችላትን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የሶሻል፤ የንግድና የገበያ ግንኙነትን ማመቻቸት፤ የጋራ መከላከያ ውል መፈራረም፤

- ከሱዳንና ከኤርትርያ ጋር በመሻረክ ፤ በምሥራቅ አፍሪቃ ታላቅ የኮኖሚና የፖለቲካ ኀይል ( ፐሎክ ) መፍጠር፤

- በሂደትም፤ የሱዳን፤ የትግራይና የኤርትርያን ኮንፌደራሲዮን ( ኮንፈደሬሽን ) ማመቻቸት፤ ማዘጋጀት፤

- ሌላውን የኢትዮጵያ ግዛት ነዋሪ፤ በዘር፤ በሃማኖትና በቋንቋ ከፋፍሎ እርስ በእርሱ እንዲበላላና እንዲጠፋፋ በማደረግ፤ የትግራይን መገንጠል ዋስትና- መተማመኛ ሊያገኝ የሚችለውን ሁሉ ተግባር መፈጸም። ዐባይ/ታላቋ ኢትዮጵያ መኖር የማትችልበትን ሁኔታ ሁሉ ማደረግ፤ ተቆራርጣና ተሰነጣጥቃ የምትቀረዋ ኢትዮጵያ፤ በደካማነቷ እንኳ ቢሆን፤ በሰላም እንዳትኖር፤ " የ 100 ዓመት ቦምብ መቅበር" ። ኢትዮጵያውያንም ፤ ፈንጅ ረጋጭና ጠራጊ ሆነው የመኖር ዕዳላቸውን ማረጋገጥ።

- በግዛት ማስፋፋት የተገነባችው ትግራይ፤ በሁሉም አቅጣጫ፤ ከውጭ መግቢያ ኮሪዶርና ከውስጥ መውጫ በረንዳ እንዳታጣ፤ በምዕራብ ሱዳን ፤ በምሥራቅ ጅቡቲ፤ በሰሜን ኤርትርያን ማዕቀፍ ያደረገ፤ የውጭ ጉዳይና የመከላከያ ፖሊሲ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ዎያኔዎቹ አምነውበታል። ዕምነታቸውንም ወደ ተግባር ለመለወጥ፤ በሁሉም አቅጣጫ ተግተው ይሰራሉ።

- ለአንድ ሀገር ዕድገትና ልማት አስፈልጊ ከሆኑት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል የሠለጠነ የሰው ኀይል መሆኑ ያከራክርም። የሠለጠነ የሰው ጉልበት ማግኘቱን በሚገባ የተረዱት የወያኔ መሪዎች፤ ነገ ለሚፈጥሯት ነጻ ሪፑብሊክ ትግራይ፤ የሚያገለግል መጠነ -ሰፊ የተማረ ኀይል በመገንባት ላይ ናቸው። በኢትዮጵያ ስም ከውጭ በሚያገኙት የነጻ ትምህርት ዕድል ( ስኮላርሽፕ) ከድኅረ- መረቃ በላይ ያለውን ከፍተኛ ደርጃ ትምህርት፤ ለራሳችው ሰዎች በገፍ ያድላሉ። በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ታላላቅ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የህክምና ዶክቶሮች፤ ነርሶች፤ መሃዲሶች፤ የኮምፒዉተርና የኤሌክትሮኒክስ ባለሙያዎች፤ ሃይድሮሎጂስቶች ( የውሃ ጥናት ጠበብቶች) የአፈር ጥናትና ምርምር፤ ወዘተርፈ. እየላኩ ያስተምራሉ። ሁሉም ነጻውን የትግራይ ሪፑብሊክን ለመገንባት የተዘጋጁ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ድምር ውጤት፤ የትግራይን ክፍለ ሀገር ወደ ታላቋ ትግራይ ሪፑብሊክ ለውጦ አዲስ ሀገር መፍጠርና ታላቋን ኢትዮጵያን ከምደረ-ገፅ ደምስሦ ዙሪያውን በባላንጣዎቿ የተከበበች፤ ሚጢጢና ምስኪን መሬት ከምስኪንና ተስፋ-ቢስ ዜጎቿ ጋር ሽብቦ ማስቀመጥ ይሆናል።

ወያኔና ሱዳኖች፤ ባለፈው ስምንት መጀመሪያ ላይ አዲስ አበባ የተፈራረሙት የጋራ መከላከያ ውል ስምምነት ፤ በሀገራችን ግበዐተ-መሬት ሂደት ውስጥ የሚካሄድ ርምጃ ነው። ይህ ሂደት የመጀመሪያው ክፍል እንጅ የመጨርሻው አይደለም። በርካታ የተጠበቁና ያልተጠበቁ ሁኔታዎችና ክስተቶች ቢፈራረቁም፤ ኢትዮጵያን የማዳከሙና ወያኔን የማጠናከሩ ሂደት እየተጠናከር መቀጠሉ አይቀርም።

በዓለም ታሪክ፤ ታላላቅ የሚባሉ ሀገሮችና ሕዝቦች እንዳልነበሩ ሆነው በሂደት መክሰማቸው የሚካድ አይሆንም። ኢትዮጵያ ሀገራችንም የዓለም ኅብረተሰብ አባል እንደመሆኗ፤ የዓለም ሂደት ከሚያመጣው ክስተት ነጻ የምትሆን አይሆንም። ከተቃጣባት የጎልውና አደጋ ለመከላከል በመፍተሄው ፍሊጋ፤ የአንድነት ኀይሉ ካልተረባረበ፤ የኔ ሀገር ነች የሚላት ሀገሩና እኔ ነኝ የሚለው እኔነቱ፤ የጠላቶቹ ጎርፍ እያሳሳቀ እንደሚውስዳቸው መረዳት ብልኅነት ነው። ጉርፍ እያሳሳቀ መውሰዱን ደግሞ፤ ያየውና የተመለከተው ያውቀዋል። ይህ ሊሆን አይችልም ብሎ መዘናጋትና እጅ-እግር አጣጥፎ መቀመጥ፤ እንዝህላልነት ብቻ ሳይሆን፤ በራስና በሀገር ላይ የሞት ፍርድ መፍረድ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !